## የጋዜጠኝነት ሚና …

በአንድ ወቅት በአዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ሁሉም ዲፓርትመንቶች እርስ በእርሳቸው ውድድር አዘጋጅተው ነበር፡፡ ውድድሩም ዲፓርትመንቶቹ ለሃገራችን ያላቸው ፋይዳ መሠረት በማድረግ እንደነበር ፈላስፋውና ደራሲው ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ከፃፈው መጽሐፍ አንብቤ ነበር፡፡ ተወዳዳሪዎቹ የራሳቸውን የትምህርት ክፍል / ፊዚክስ፣ ኬምስቲሪ፣ ሂሣብ፣ ባዮሎጂ፣ ፍልስፍና፣ ሶሲዮሎጂ፣ጤና ሳይንስ፣ ኢኮኖሚክስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ወዘተ…/ በመወከል የመከራከሪያ ሃሣባቸውን በማቅረብ ተፎካክረው ነበር፡፡

እነዚህን የትምህርት ዓይነቶች የወከሉት ተወዳዳሪዎች የእኔ ይበልጣል፣ የለም የእኔ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነው፣ የእኔ ወቅታዊዉን የኢትዮጵያ ችግር ፈቺ ነዉ… እያሉ ሲከራከሩ ጋሼ " ስብሃት ለአብ" የኢጁኬሽን የትምህርት ክፍል በመወከል ያቀረቡት ሃሣብ ሁሉም ለሃገራችን ዕድገት ብልፅግና እንደየአስፈላጊነታቸው ጠቀሜታ አላቸው ብለዉ ተከራከሩ ፡፡ ነገር ግን ሌሎች የትምህርት ክፍሎች እንቁላል ሲሆኑ የኢጁኬሽን ትምህርት ክፍል ደግሞ በዶሮ ትመሰላለች፡፡ ሁሉንም ትምህርት ትፈለፍላቸዋለች በማለት ነበር አሸናፊ ሆነው የተሸለሙት፡፡

አነሳሴ ዲፓርትመንቶችን ለማወዳደር ሳይሆን የጋዜጠኝነት ሚና በኢትዮጵያ ምን ይመስላል የሚለውን ከታዘብኩት ላካፍላችሁ ነው፡፡ ከወዲሁ ከይቅርታ የምጠይቀዉ ነገር ቢኖር የተለየ የአፃፃፍ ክህሎት ወይም የጋዜጠኝነት ሙያ ኖሮኝ ሳይሆን የታዘብኩትን ለእናንተ ለማካፈል ነዉ፡፡

ጋዜጠኝነት ወይም ሚዲያ ለህብረተሰቡ ማበርከት ያለበት ነገር ቢኖር ጥራታቸዉን የጠበቁና ተዓማኒነት ያላቸውን ዜናዎች፣ መረጃዎች፣ ትምህርቶችን እና መዝናኛዎችን ለሕብረተሰቡ ማቅረብ ነበር፡፡ ነገር ግን በሀገራችን የምንመለከተዉ አዝማሚያ ከዚህ ተቃራኒ እየሆነ ይመስለኛል፡፡

ፋይናንሺያል ታይምስ ከተባለውና በስፋት ተነባቢ የሆነው የእንግሊዝ ጋዜጣ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር በወርሃ ሰኔ ውስጥ ቃለ ምልልስ አድርጎ ነበር፡፡ ከቃለምልልሶቹ መካከል የጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን መልቀቅ ጉዳይ አንደኛው ነበር፡፡ ከጋዜጣው ድረ ገፅ እንደተመለከትኩት የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ስልጣን የመልቀቃቸውን ጉዳይ ለፓርቲያቸው ሃሣብ ማቅረባቸውንና የፓርቲውን ውሣኔ እየጠበቁ መሆናቸውን ነበር የገለፁት፡፡ በተጨማሪም የፓርቲውን ውሣኔ የማይቀበል ግን ካለ ፓርቲውን መልቀቅ እንዳለበት ተናግረው ነበር፡፡

አብዛኞቹ የሃገራችን ሚዲያዎች ግን ይሄንን በሌላ መንገድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ፓርቲዬን እለቃለሁ” ብለዋል ብለው መረጃው ከተሸጠ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትሩ “ፓርቲዬን እለቃለሁ” አለማለታቸውን ስሰማ የፋይናንሻል ታይምስን ሙሉ ዘገባ ተመልክቸ በሁኔታው እጅግ አዝኘ ነበር፡፡ሆን ተብሎ የተዛቡ ዘገባዎችን ማቅረብ የጋዘጤኝነት ሙያ የሚፈቅድ አይመስለኝምና፡፡

ለነገሩ አንዳንዶቹ ጋዜጦች በፊት ገፃቸው “ከገጽ 2-3 ይመልከቱ” በማለት የሚያቀርቡትን ትንተና በጉጉት ገልጠን ስንመለከት ውስጣቸው በውሸት የምሁር ትንተና (pseudo intellectual Analysis) ፣ ከመዝገበ ቃላት በተወሰዱ የቃላት ትርጉሞች ማንነታቸው ወይም መጽሐፋቸው የማይታወቅ ሁሉ የምሁራን ትንተና በማስመሰልና ስማቸዉ እንዲጠቀስ ያልፈለጉት አቶ እገሌ ወዘተ… በማለት እያቀረቡ ጋዜጣቸውን መሙላት የተለመደ አሰራራቸው ወይም “ኤድቶሪያል ፖሊሲያቸው” ይመስላል፡፡

Conflict of Interest (የጥቅም መጋጨት)

በሃገራችን የጋዜጠኝነት ሙያና የፖለቲካ ዝንባሌ መካከል ያለው መስመር የደበዘዘ ሳይሆን የጠፋ እስኪመስል ድረስ ዘገባዎች ሚዛናዊነት ጎድሎአቸው ይታየኛል፡፡ መስከረም ላይ የጋዜጠኝነት ፕሬስ ካርድ ተመዝግቦ ይወስዳል፣

ግንቦት ላይ ደግሞ የምረጡኝ ቅስቀሳውን ለማካሄድ ቀበሌ ይሰለፋል ፡፡ይህ እንዴት የነፃ ፕሬስ ዘጋቢ ሊሆን ይችላል?

ስለ አንድ ፓርቲ አመሰራረት፣ የውስጥ አደረጃጀት፣ የፓርቲዎቹን አመራሮች /ለምሳሌ የአንድነትን ወይም የኢዴፓ/ በጥልቀት የሚያውቅ ጋዜጠኛ ስለፓርቲዎቹ ጥንካሬ እና ደካማ ጎን በመተንተን ለሕብረተሰቡ ትክክለኛ መረጃ ቢያቀርብ የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡

የጥቅም መጋጨት የሚመጣው ጋዜጠኛው የአንድነት ወይም የኢዴፓ ፓርቲን ወይም አንዱን ደግፎ አንዱን የሚጠላ ከሆነ የጋዜጠኛው ዘገባ ወይም የሚዲያው ተቋም ተዓማኒነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ በተግባር ግን ሲታይ የጋዜጠኞቻችን የፖለቲካ አስተሳሰባቸው በሙያቸው ላይ ተፅዕኖ እየፈጠረ ያለ ይመስላል፡፡ የሚዲያዎቹ መስራቾችም ቢሆኑ ለነገሩ አንዳንዶቹ ከእነ አፈጣጠራቸው ጀምሮ በጦርነቱና በአስተሳሰብ ትግሉ ውስጥ ተሸናፊ የነበሩና የፕሬስ ነፃነት መታወጅን ተከትሎ የተፈጠሩ መሆናቸው ይታወቃል ፡፡ በሥርዓት ለውጥ ምክንያት ጥቅሙ የጎደለበት የሚዲያ ተቋም ብዕር ምን ሊተፋ እንደሚችል መገመት አያስቸግርም፡፡ ግን እስከመቼ አስተሳሰባቸውን በነፃው ፕሬስ ላይ ከዚያም አልፈው ትክክለኛና ወቅታዊ ኢንፎርሜሽን ፈላጊው ሕብረተሰብ ላይ ይጭናሉ? ነዉ የኔ ጥያቄ፡፡

***ብሔራዊ ጥቅም***

አንድ ሚዲያ ሲቋቋም በዋናነት ሊኖረዉ የሚችለዉ ዓላማ ማሳወቅ ፣ማስተማርና ማዝናናት ነዉ፡፡ መኮንን ብሩ የተባሉ በጥናታቸዉ እንደገለፁት በተለይ በታዳጊ ሀገራት አንጻር ሲታይ ሚዲያ ልማትን ለማፋጠን ፣የደሞክራሲ ስርዓት በመገንባት ፣አንድነትን በማጠናከር በኩል ያለዉ ሚና ከበለጸጉት ሀገሮች ሚዲያ ተልዕኮና ባህርይ ለየት ማለት አለበት ይላሉ፡፡የታዳጊ ሀገር ሚዲያ በምንም ሁኔታ “Bad news is good news” ወይም “blood deserves lead” የሚለውን የምዕራባዊያን ሚዲያ አመለካከት ሙሉ በሙሉ በመጋራት በዋናነት ሁከት፣ አሰደንጋጭና

አሰቃቂ ክስተቶች ላይ እያተኮሩ ድርጊቶችን ብቻ እየመረጡ መዘገብ የለባቸዉም፡፡

የሆነ ሆኖ አሜሪካኖች በማንኛውም አስተዳደር ወቅት /በክሊንተን፣ በቡሽ ወይም በኦባማ/፣ በየትኛውም ችግር ወቅት /የኢኮኖሚ ዝቅጠት ወይም ቀዉስ፣ በርድ ፍሉ ወይም ስዋይን ፍሉ መከሰት፣ መብራት በአጠቃላይ ቢጠፋም (Black House Day) ወዘተ/ ስለሀገራቸው መጥፎ ገጽታ ማንሳት አይፈልጉም፡፡ ይሄን ሲል ገጽታቸውን በማይጎዳ መልኩ ኢንቨስትጌቲቭ ጋዜጠኝነት አይሰሩም ማለት አይደለም፡፡ የክሊንተንና የሞኒካን የጓዳ ጣጣ እንኳን ሳይቀር ወደ አደባባይ አውጥተዋል፡፡ነገር ግን የአሜሪካንን የሊብራል ሪዕዮተ ዓለም የበላይነትን አስተሳሰብን የሚቃረን ዘገባ ግን አይታይባቸዉም፡፡

በእኛ ሀገር ግን ያሉት ጋዜጠኞች በረሃብ፣ በጦርነት፣ በቸነፈር የሚታወቀውን ገጽታችንን በዛሬዉ እዉነታ በመቀየር በበጎ ጎኑ እንገንባ ሲባል የኢትዮጵያን ገጽታ መገንባት አይችልም በማለት የ77ቱን የተራበ ኢትዮጵያው ልጅ ፎቶ በፊት ገፃቸው ይዘው ይወጣሉ፡፡ ይሄ የስንቱን በውጭና በሃገር ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ የሚያሸማቅቅ ክስተት መሆኑን መረዳት ተስኖት ሳይሆን የፖለቲካ አስተሳሰቡ የሚታየውን ልማት ለመቀበል ስለሚያስቸግረው ነው፡፡ ከዚያም ከየት ያመጣው ምሁር እንደሆነ የማይታወቅ ይጠቅስና ገፅታ መገንባት እንደማይቻል የተለመደውን ትንተናውን ያክልበታል፡፡

ብሔራዊ መግባባት ደግሞ የሃገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሃገራዊ የጋራ አጀንዳ በሆኑ በልማት፣ በሰላምና በዲሞክራሲ ሥርዓት በግንባታ ላይ የጋራ አስተሳሰብ መያዝና መረባረብን ይጠይቃል፡፡እያንዳንዱ ዜጋ በሰራዉ መጠን ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል-ብሄራዊ ጥቅም በዚያዉ ልክ ሊረጋገጥ ይችላል የሚል መግባባት ላይ መድረስ ነዉ ፡፡ አንዳንዶቹ ሚዲያዎች ብሔራዊ መግባባትን ሂደት ማጎልበትና በመሠረታዊ ጉዳዮችና ሃገራዊ መግባባት ላይ የደረሰች ኢትዮጵያን እውን ከማድረግ ይልቅ በየጊዜው የሕዝቦችን አንድነት የሚያናጉ ቁርሾዎችንና ያለፈውን የተዛቡ ታሪኮችን ፈልፍሎ በማውጣት የመግባባት ሂደቱን

ረጅም እያደረጉት ይገኛሉ፡፡ለእነሱ ብሄራዊ መግባባት ትርጉሙ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ስልጣንን ለተቃዋሚ ማጋራት ነዉ ብለዉ ስለሚያምኑ ለብሄራዊ መግባባት የብዕራቸዉ ቀለም ይደርቃል ፡፡

የሃገራችን ሕዝቦች አንድነት ባልተጠበቀበት እና የውስጥ ችግሮቻችን ባልተፈቱበት በሀገር እንዴት እድገት ሊመጣ ይችላል? እንዴት የውጭ ኢንቨስትመንትን መሳብ ይቻላል? እንዴት ቱሪስት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል? የሀገር ውስጥም ባለሃብት እንዴት ሃብቱን በሀገሩ ኢንቨስት ያደርጋል?

መቀመጫቸውን ሶማሊያ አድርገው በኢትዮጵያ ላይ ወቅታዊና ቀጥተኛ የደህንነት አደጋዎችን በደቀኑበት ወቅት እንኳን አንዳንድ የሃገራችን ሚዲያ ከሌሎች የኢትዮጵያ ደህንነት ደንታ ከማይሰጣቸው ሚዲያዎች ጋር እኩል ዘገባችን ምን እንደሚመስል ዞረን ብናይ ትዝብት ነው፡፡ ይሄ ሁሉ የብሔራዊ ጥቅምን መዘንጋት ለርካሽ ፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ ፡፡

## <u>የህዝብ ፍላጎት</u>

የአሁኑ የጋዜጦች አካሄድ የሕዝቡን ፍላጎት ያገናዘበ ነው ማለት ይከብደኛል፡፡ ይህን ለማለት ያስደፈረኝ መቀመጫቸው በአዲስ አበባ የሆኑ ሚዲያዎች ከሚሸፍኑት ዘገባዎች ውስጥ በኢትዮጵያ የረግቢ (Rugby) ጨዋታ በጃንሜዳ መጀመሩ ነበር ከፍተኛ ተነባቢነት ያገኘዉ፡፡ በአንፃሩም በእኔ አመለካከት በማደግ ላይ ያሉት ሃገሮች የሚገኙ ሚዲያዎች ልማትን በማፋጠን የዲሞክራሲ ባሕሉን በማጎልበት ሰላምና መረጋጋትን ማዳበርና ማጎልበት በሚችሉ ሥራዎች በአጠቃላይ የአዳጊ ሃገር የጋዜጠኝነት የሙያ (Development Journalism ) የተጠመደ ቢሆን በህዝቡ ዘንድ የተመረጠ ይመስለኛል ፡፡

የሕዝቦችን አንድነት ማስጠበቅ የሚያስችልና ልዩነታቸውን የማያከብርላቸው ሚዲያ ካልጎለበተ አንድ የጋራ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር ልንወጣው የማንችለው ተራራ ሊሆንብን ይችላል፡፡ የሃገራችን ሕዝቦች ፍላጎትም የእድገትና የሠላም ዜናዎችን አጋጅ የሀብትና የቆመጠጠ ዜናዎችን መስማት እንደሚፈልግ

ሚዲያዎቹ ራሳቸው ከስርጭት አድማሳቸው (Circulation) ለምን አነስተኛ እንደሆነ ራሳቸውን ቢጠይቁ ጥሩ ነው፡፡

<u>ሚዛናዊነት የጎደለዉ</u>

ዳኛ ስለ አንድ በፍርድ ሂደት ስላለው ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ለመስጠት ግራና ቀኝ አይቶ የሕገ መንግሥቱን የበላይነት ባረጋገጠ መልኩ ፍርዱን ይሰጣል፡፡ ጋዜጠኛም ስለአንድ ክስተት ሽፋን ሲሰጥ ሚዛናዊነቱን ጠብቆ ከአድሎአዊነት ነፃ በሆነ መልክ ለሁሉም የመናገር እድል ሰጥቶ መሆን አለበት፡፡

ነገር ግን በሃገራችን ያሉት ሚዲያዎች ሚዛናዊነት መጠበቅ የሚያስችል አስተሳሰብ ከእነ አፈጣጠራቸው የተላበሱት አይመስልም፡፡ ስለአንድ ግለሰብ ወይም የሐይማኖት መሪ፣ የሃገር መሪ የመሳሰሉትን በተመለከተ የሚያቀርቡት ዘገባ ሚዛናዊነት ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ክብርና ሞገስ የሚነካ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የግለሰብን ክብር የሚነካ ብቻ ሳይሆን የሃገርን ክብር የሚጎዳ መስሎ ይታየኛል፡፡

ለምሳሌ በቅርቡ በቤተክህነት አካባቢ የተከሰተውን አለመግባባት መሠረት በማድረግ የሚዘገቡት ዘገባዎች በመሠረተ ቢስ ውንጀላዎች የተሞሉ መሆናቸውንና አድሎአዊነት የሚታይበት ይመስላል ፡፡ በተለያየ ጋዜጦች የሚወጡት መረጃዎች የተለያየ መሆናቸው ደግሞ ዘገባው ተዓማኒነት ጥያቄ ዉስጥ እንዲህ አይነት የጋዜጠኝነት ሚና ጉዳዩን ከማባባስና በሕዝቡ ወይም በምእመኑ ውስጥ ውዥንብር ከመፍጠር ውጭ መረጃን ለሕበረተሰቡ የማዳረስ ሚና አይኖራቸውም፡፡ ከአድሎአዊነትና ከቅድመ ጥላቻ (Prejudice) ነፃ የሆኑ የነፃ ፕሬሶች በዕውቀታቸው እና በአመራርነታቸው የተከበሩት የሃገር መሪዎችን በማጥላላት እና ክብራቸውን በሚነካ ዜማዎች የተሞሉት ዘገባዎች የዜጎችዋን ክብርና ሞገስ ብቻ ሳይሆን የሃገርን ክብርና ሞገስ የሚነካ ይሆናሉና ቢታሰብበት፡፡

*<u>የሙያውን ክብር የሚነካ</u>*

ይህን የተቋሞችንና፣ የግለሰቦችን ክብር የሚነካ ዘገባ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በግል ወይም በቡድን ተቃውሞ ሊያስነሳ እንደሚችል መገመት ይቻላል ፡፡ አሁን እየታዩ ያሉት ክስተቶች ይሄን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ እየተባባሱ የመጡት ህገ ወጥ ድርጊቶች የሚወገዙና ወደ ህግ መቅረብ ያለባቸዉ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ ጋዜጠኞች ከአድሎአዊነት፣ የሃገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ከሚጎዳና የሃገርን ክብርና ሉአላዊነት ከሚነካ ሥራ ራሳቸውን መቆጠብ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ የሕብረተሰቡን ፍላጎትና የሃገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ የጋዜጠኝነት ሙያ መበረታታትና መደገፍ አለበት በማለት እሰናበታለሁ፡፡

ተመስገን ሞ.

በፅሁፉ ላይ ያለዎትን አስተያየት tmotuma@yahoo.com